መረጃ፡ መለዋወጥ፡ ያሰጠነገን፡ ለማወቅ፡ እደደሳም፡ እንገኛን፡ ይህን፡ መረጃ፡ ቢያንስ፡ ለሚያውቋቸው፡ እያሰሙ፡ ሰዎች፡ ያስተላልፉ!!!

# አስቸኳይ ጥሪ ለአማራ ተወላጆች በሙሉ!!

ወያኔ በአማራው ላይ ያለው ጥላቻው ፍርሀት ላይ የተመረኮዘ ነው። አማራው በኢኮኖሚና በድርጅት ተጠናክሮ መገኘት የለበትም የሚል ጠንካራ አቋም አለው። ለዚህም የአማራውን ግዛት በመበጣጠስ፤ የተረፈውን ደግሞ በአገውና በኦሮሞ ዞኖች በመከፈል በውስጡ የርስበርስ ግጭት እንዲያናጋው በማድረግ አማራዉን ማዳከም ወሳኝ መሆኑን አምኖበታል። ከመጀመሪያው ስልጣን ሲይዝ አማራውን መሳሪያ አስፈትቷል። በሌሎቹ የዘር ክልሎች አማራውን አስመትቷል። እስካሁን ድረስ ካገራችን ውጣ ወደ መጣህበት ተመለስ በመባል መግቢያ መውጫ አጥቶ ደሙን ባፈሰሰላት አጥንቱን በከሰከሰላት ኢትዮጵያ ነፃነቱን ተገፎ ስደተኛና 2ኛ ዜጋ ሆኖ እንዲኖር ተገዷል። ወያኔ/ኢሕአዴግ በአማራው ላይ ካደረሳቸው በደሎች በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው፤-

፩ኛ-

የዕድገትና ልማት ተቋሞች ዝርጋታ ከሌሎቹ ክልሎች ባነሰ እንዲካሄድበት ማድረግ ዋነኛ አቋሙ ነው።

፪ኛ- ጎንደርን ለማጥፋት

ሀ፦

ታች አርማጭሆን፣ የሳንጃ፣ የመተማና ቋራ ለም የሆኑና ነዳጅ ዘይት ያለባቸው መሬቶችን ለሱዳን አስረክቧል። አቀናባሪዎቹ ስዩም መስፍን፣ ዶ/ር ተቀዳ አለሙ፣ ፍስሀ ይመር፣ አዲሱ ለገሰ፣ ደመቀ መኮንንና በረከት ስምኦን ሲሆኑ የታዘዙትም በመለስ ዜናዊ ነው።

ለ፦

ሁመራን፣ ወልቃይትና ጠገዴን ለም መሬቶች ከመቀላቀሉ በተጨማሪ ትግራይ ከነዚህ የአማራ መሬቶች ከፍተኛ የወርቅ ማዕድን ባለቤትም ሆናለች። የራስዳሽን ተራራና አብዱራፌን ለመውሰድ ጣልያን ከሰራው በደል በከፋ በአማራው ላይ ካስቀመጣቸው የብአዴን ጉደይ አስፈፃሚዎቹና ወኪሎቹ ጋር ሕጋዊነት ባለው ሁኔታ የተሰጠው እንደሆነ የሚያመለክት ሰነድ ለመፈራረም ሽርጉድ ማለት ጀምሯል። አማራው ሳያውቀው ደመቀ መኮንን ጉዳዩ በምስጢር እንዲያዝ ትዛዝ ሰጥቷል። ይኼው ግለሰብ በት/ትሚኒስትርነት ስልጣኑ ተጠቅሞ በ፯ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ራስ ዳሽን ትግራይ ውስጥ እንዳለ ተደርጎ እንዲዘጋጅም አድርጓል። ***"በጡህ ላይ ቆሮቆር"*** በሆነ ወንጀል አማራው ባደባባይ ሲዘርፍ ካብራኩ የተገኛችሁ ምሁራን እስከ መቼ ድረስ በምን አለብኝነት ርቃችሁ መኖር ትሻላችሁ።

ሐ፦

በጣና በለስ በሚለማው የስኳር ፋብሪካ ግንባታ በአለፋ ወረዳ ቢሆንም ንብረትነቱ የኤፈርት በመሆኑ ከጎንደር ከመቶ ሺህ በላይ ሄክታር ተቆርጦ አዲስና ጃዊ ወረዳ በሚል በ፪ሺ፪ በማቋቋም ወደፊት ከአማራው አውጥቶ እንደ አገር ሊፈጥረው በሚያዘጋጀው አዊ ዞን ውስጥ አካቶታል። በዚህ ሸፍጥ ከጎንደር ሀያ ሰባት ቀበሌዎች ተወስደዋል። አቀናባሪዎቹ ወያኔው አባይ ፀሀዬና የብአዴኑ ወኪላቸው ደመቀ መኮንን መሆናቸው ታውቋል። ለመሆኑ ቆጋ በሚባለው የመስኖ ልማት

ከ፯ሺ ሄክታር ፰ሺው በኤፈርት ለትግራይ ሀብት ማፍሪያ ተይዞ በመታረስ ላይ እንደሆነ ስንታችሁ ታውቃላችሁ።

፫ኛ-

አላማጣን ከወሎ ገንጥሎ ትግራይ ጓዳ ውስጥ ያስገባው በጥጥ ምርት ወዘተ. አማራውን ለም መሬት ለማሳጣት ነው። ወደፊትም ካሳ ተ/ብርሀን በተባለ ወያኔ የብአዴን ካድሬ ዋግን ጠቅሎ ለትግራይ ለመስጠት ***"የአፄ ካሌብ ልጆችና የአሸንዳ/ ሻዴይ"*** ባህል ከአማራው ሳይሆን ከትግሬዎች ጋር ያቀራርበናል የሚል አቋም ይዞ መንቀሳቀስ ጀምሯል።

፬ኛ-

በተከዜ፣ በከሰም፣ በጃማ አማራው እንዳይጠቀም በውሀና ግብርና ሚኒስቴር መስርያቤቶቹ በኩል ለህይልና መስኖ ወንዞቹ በትግራይ፣ በኦሮሞና በአፋር ተገድበው ባለንብረቱ አማራ መና ቀርቷል።

፭ኛ-

አባይም ቢሆን ግድቦቹ የሚገነቡት በቤኒሻንጉልና በነቀምት አካባቢ ኦሮሞ ውስጥ ነው። ወደፊት አገራቱን መገነጣጠል የሚሻው ወያኔ አማራው በአባይ እንዳይጠቀም በቅጥረኞቹ ምሁረት ደበበና አለማየሁ ተገኑ የኦህዴድ ቀንደኛ ፀረ አማራ ወኪ ሎቹ ያስነደፈው ዕቅድ ነው። ሰዎቹ እሮሞ ውሰጥ ቤካ አቦ የሚባለው ሁለ ገብ ፕሮጀክት ጥናት ተጠናቀ በወያኔ ተጨማሪ ግድብ ስለሚሰራ አይዞህ ባይ አልባ አማራው ***"እፍንጫህን ላስ"*** መባሉ አንጀታቸውን እነዳራሰው በኦህዴድ ስብሰባ ላይም መናገራቸው የቆሙት አማራውን በስልጣናቸው ተጠቅመው ለማውደም እንደሆነ ተረጋግጧል። በአሸከርነት የሚታወቁት ጥቂት አማራ ነን ባዮችም በዝምታ ወይም በተባባሪነት አብረው ተፈርጀዋል። በመሰራት ላይያሉት የሬብና መገጭ ግድቦችም ከሚያለሙት ግማሹ ከአስር ሺህ ሄክታር በላይ ለኤፈርት መመደቡን፣ ከጢስ አባይ የሚገኘው ሰማንያ ደግሞም የተከዜ ሶስት መቶ ሜጋዋቶች ወደ ብሄራዊ ማከፋፈያ ሳይገቡ በቀጥታ ትገራይን ብቻ እንደሚያገለግሉ ታውቃላችሁ? ጢስ አበይ የደረቀው የወያኔን ጥቅም ለማስጠበቅና አማራውን ቆሽቱን ለማድበን ነው። ህይወት ያለው ሁሉ በምግብና ጤና ራሱን ከበደለ ትርፉ መኮስመንና በቀላሉ ለበሽታ መጋለጥና መሞት ብቻ ነው ዛሬ የጣና ሀይቅ ዕጣ ፋንታ ይሄው ሆኗል። ተፈጥሮ የሸለመው የጎኑ ግድግዳ በወያኔ ተንዶ ዛሬ በአባይ የሚኮበልለው ውሀ ሳያንሰው የበለስን ሀይል እንዲያመነጭ ብሎም የሸንኮራ መስኖ በማልማት ለኤፈርት ሀብት ማጋበሻ ውሏል። ልብ በሉ የበለስ ወንዝ ሚና መስኖው ላይ ብቻ ሲሆን ሙሉ ሀይል የማመንጨቱ ሀላፊነት የምስኪኑ ጣና ነው። ይህም የሀይቁን ዕድሜ ማሳጠር ነው። ሌላውም ጣናን የሚመግቡት ጅረቶች ሬብና መገጭም በመገደብ ወያኔን ለማገልገል እየተዘጋጁ ነው። ጣና ስለሚራብ ደረጃ በደረጃ ወደ ኮስማናነት ተለውጦ በመጨረሻ ዕጣ ፋነታው ሞት ብቻ ይሆናል። የህዳሴው ግድብ እኮ ይህን ሀቅ ተመርኩዞ ግብፅና ሱዳን ጥቅማቸው በጣና ጥፋት እንዳይጓደል በአሽከራቸው በወያኔ የተቀነባበረ አማራውን ቅስሙን ሰብሮ የማጥፋት ፋሽስታዊ ወንጀል ነው። ባህርዳርም ዕጣዋ እንደጣና ይሆናል። ዛሬ አገር ቤትያለን ሁሉ ጆሮአችንና ዓይናችን በአባይ ፕሮፓጋንዳ ዝሏል ኪሳችንም ከኑሮው ውድነት ሌላ ተገደን በምናደርገው መዋጮ ባዶ ሆኖብናል። አባይ ይገደብ ግን ጥቅሙንና

ጉዳቱን ብአዴን ለአማራው አዛብቶ ስለሚነግረው ሞኙ አማራ በባዶ ሜዳ ባለ በሌለ አቅሙ ድጋፉን ቀጥሏል። ***"ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት"*** ሆነና አማራው አሁንም እንደጥንቱ በአዝማሪ ግጥም የህዳሴውን ግድብ ያወድሳል። አገርህ የአባይ መፍለቂያ እየተባለ በዶኩሜንተሪ ፊልሞች ተብነሽንሿል። በወያኔ ካድሬነት የሚታወቀው ለገሰ ቱሉ የተባለ ኦሮሞ በአማራው ክልል ለሚነዛው አሳሳች ፕሮፓጋንዳ ከበረከት ስምኦን በሚሰጠው መመሪያ በአማራ መገናኛ ብዙሀን ውስጥ ባሰባሰባቸው ሌቦች ትግሬዎችና ኦሮሞዎች ጋዜጠኞች በኩል ያስፈፅማል። ነገሩግን ***"ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ"*** ነው።

፩፦ ጣናን ደርቆ የገጠጠ ባዶ መሬት ለልጆቹ ያስተላልፋል።

፪፦ የአባይ ወንዝ ተጨማሪ ግድብ ለዚያውም ሁለገብ የተባለና ከ፪ሺ ሜጋዋት በላይ ሀይል የሚያመነጭ በወለጋ ይገነባል።

፫፦ አማራው እንደልማዱ አይዞህ ባይ በማጣቱ እጁን አጨብጭቦ ሙልጩን ይቀራል። ብአዴን በአማራው ላይ ዛሬ፣ ነገ፣ ተነገድያ፣ እስከ ዓለም ፍፃሜ የሰራቸው ጥፋቶች ከታሪክ መዛግብት አይፋቁም። ዛሬ በአማራው ክልል ቁልፍ ስልጣን ለይ የተቆናጠጡት አልፎ አልፎ በስማቸው የሚታወቁ በአመዛኙ ግን የአማራ ስም ያጠለቁ ትግሬዎችና ኦሮሞዎች ናቸው። በክልሉ ያለውን ፖለቲካ የምናውቀው በወያኔና ሻቢያዊ ኦነግ በኩል ምስጢራዊ ኢትዮጵያን የማጥፋት የስራ ቅንብር ስለመኖሩ የክልሉን ፈላጭ ቆራጮች እነማ እንደሆኑ በማጋለጥ የአማራ ምሁራንም የግል የቤት ስራ ከሰራችሁ የምነግራችሁን ሀቅ አደባባይ ማውጣት ትችላላችሁ። ዋነኛው ጥያቄ የወያኔና የኦነግ ካድሬዎች አማራን ወረውና ካብራኩ የወጡ በመምሰል በቅኝ አገዛዝ ውስጥ ባገሩ እንዲረግጡት የተደረገው ለምንድነው? መልሱን ለአማራ ምሁራን ትቻለሁ። አሁንም ወያኔና ኦነግ ጠበኞች ናቸው የምትሉ ከሆነ እኛ ጭቁኖቹ የምናስታውሳችሁ ***"ያልጠረጠረ ተመነጠረ"*** ከሚለው አነጋገር ትምህርት እንድ ትወስዱ ነው። ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ነብሳቸውን ይማርና ለማስማርና ለማስጠንቀቅ የሞከሩት ይህንኑ የጉዶች ጉድ ከጥንስሱ ለማኮላሸት ነበር። ሆኖም ሰሚአጥተው ጅሮ ዳባ ተባሉ። ነገር ግን የከፈሉት መሰዋዕትነት አሁንም ቢሆን ለአማራው የተስፋ ጧፍ ሆኖ በመንደድ ተከተሉኝ ተደራጅታችሁም እያጠፏችሁ ያሉትን እንደ ንብ ዘማችሁ አዋርዷቸው የሚል ጮራውን መፈንጠቁን ቀጥሏል። ነገር ግን እስካሁን ተግባራዊ የሚሆንበትን ቀን ማየት አልቻልንም። የአማራ ***"ምሁራን"*** ከዚህ የበለጠ ቆሽት የሚያነድ የሕዝብ ጉደይ ስለሌለ አስባችሁ መፍትሄ ፈልጉለት። በርካታ ምሳሌዎች ልሰጣችሁ እችላለሁ። ነገር ግን ከናንተ የተሰወረና የማታውቁት የለም። አማራው ታፍኗል፣ መፈናፈኛ አጥቷል፣ ነፃነቱን ተገፏል፣ በየጊዜው የገባበት የማይታወቀው፣ የሚታፈነው፣ ዘብ-ጥያ የሚጣለው በዝቷል። ሕዝቡ በወያኔው ብአዴን በእሳት እየተቃጠለ መኖሩ ወደ፫ኛ ዜጋ ደረጃ አውርዶታል። የሚያደራጀው ካገኝ ***"ሆ"*** ብሎ መነሳቱ አይ ቀሬነው። ባጠቃላይ በተጫነበት የዘር ፖለቲካ ጭቆና ኑሮው መሮታል፣ አንገፍግፎታል። ወያኔዎች በንቄት የሚሉት ***"ተልባ ቢንጫጫ በሙቀጫ"*** ነው። ነገር ግን አማራው መሪ ድርጅት ካገኘ እሳት የነካው ***"ተልባ"*** ምን ያህል እንደሚፋጅና እንደ ሚያቃጥል በተግባር ያሳያቸው ነበር። ሆኖም ባለፉት ሀያ አመቶች ሊለወጥና ቁርጠኝነት ሊታይበት ያልቻለው የተወናበደ የአማራ ምሁራን አቋም አማራዊ ድርጅት መመስረት ባለማስቻሉ የአማራው ጀግንነት ዕውን ሊሆን አልቻለም። ሁኔታው ወያኔን ራሱ ከጠበቀው በላይ ጠንክሮ በኢትዮጵያ ላይ በዘፈቀደና በማን አለብኝነት ዳንኪራ እንዲጨፍር አድርጎታል። ይባስ ብሎ

የአማራውን ምሁር *"ሆዳም"ና ሴት ካገኘ በቃው ወኔ ቢስ ነው"* እስከ ማለት ደርሷል።

፯ኛ-

በቅርቡ በብዙ የውጭ ምንዛሪ የሚገነቡት የፋይበር ኦፕቲክስ መስመሮች በደቡብ፣ በኦሮሞ፣ በአፋር፣ በትግራይና ሌሎቹም ሲሆን አማራው አሁንም ወደፊትም ተጠቃሚ እንዳይሆን ተደርጓል። ለዚህም የመርዙ ቀማሚዎች የወያኔና ኦህዴድ ካድሬዎች ናቸው።

፰ኛ-

ቻይናና ሕንድ የሚገነቧቸው የባቡር ሀዲዶችም አማራን ዘሎ በትግራይ፣ በኦሮሞ፣ በአፋርና ሱማሌ ሲሆን መስመሮቹ ወደ ጅቡቲ ዘላቂዎች ናቸው።

፱ኛ-

በማንኛውም ክልል የማይተገበረው የቤተሰብ ዕቅድ አሻፈረኝ ያሉትን በማሰርና በማስገደድ ወዘተ... በመሳሰሉ ቅጣቶች የሚከናወነው አማራ ውሰጥብ ቻነው። ለአቅመ አዳም የደረሰች ሴት የወሊድ ማቆሚያ መድሀኒቶች ተገዳ ትወስዳለች። አማራው በአዲስ ትውልድ ራሱን እንዲተካ ስለ ማይፈለግ በብአዴን ወኪሎቹና በካድሬዎቹ የዘር ማጥፋት ወንጀል በጤና ባለሙያዎቹ መፈፀሙን ቀጥሎበታል። ለዚህም ዶ/ር ቴዎድሮስ አድህኖም ቀንደኛው የወያኔ አቀነባባሪ ነው። ምሳሌ ከፈለጋችሁ የክልሉ መንግስት ፖሊሶች ጉዳዩን በሀላፊነት በጉልበት እንዲያሰፈፅሙ በ፪ሺ፫ ያወጣውን መመሪያና በዚህም ሳቢያ በየወረዳው ውስጥ ለእስርና መንገላታት ተጋልጠው ያሉትን በርካታ ለአቅማዳም የደረሱ አማራዎች ጉዳይ መከታተል ትችላላችሁ። ባለፈው የሕዝብቆጠራ ሳሚያ ዘካሪያ የተባለችው የኦህዴድ ከፍተኛ አመራርና ቀንደኛ ፀረ አማራ የወያኔ የጥፋት መልእክተኛ በቀጥፊት የአማራውን ቁጥር ከማሳነሷ ሌላ ኤይድስ በኢትዮጵያ አማራ ውስጥ ብቻ እንደተስፋፋና ከ፪ ሚሊዮን በላይ አማራዎች በበሽታው በማለቃቸው የአማራው ቁጥር ቀንሷል ማለቷን ሁላችንም አንረሳውም።

፲ኛ-

ወያኔ በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ብሔርና በሔረሰቦች ሁሉ አማራውን እነዲጠሉና በየክልላቸው እንዲጨፈጭፉት የፖለቲካ፣ ወታደራዊና ሕጋዊ ሽፋን ስልጣን ከያዘበት ቀን ጀምሮ መስጠቱን ገፍቶበታል። ወርቅነህ ገበየሁና ሀሰን ሺፋ በሀላፊነት ይህን የዘር ማጥፋት ቅንብራዊ መሰሪ ወንጀል ያስፈፅማሉ። አማራውን ትጥቅ አስፈትተዋል። አንድም አማራ መሳሪያ በጁ እነዳይገባ ሌት ተቀን ከብአዴን ሰላዮች ጋር ክትትል ይደረጋል። መሳሪያ የተገኘበትም በተቀዋሚነት ተፈርጆ ዘብ-ጥያ ይወርዳል፣ የቁም ስቅሉን ያያል፣ ይረሸናል። ባጠቃላይ አማራ ሕዝብ ላይ በሚፈፀሙት የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ከላይ ከተጠቀሱት ወያኔዎች ሌላ ተፈራ ዋለዋ፣ አዲሱ ለገሰ፣ በረከት ስምኦን፣ ደመቀ መኮንን የተጠሉ ዋነኞቹ ግፈኞች እንደሆኑ በክልሉ ሕዝቦች ይነገራል። አያሌው ጎበዜ ምንም እንኳን ለዘብተኛና ለአማራው መልካም ያስባሉ ቢባልም ወያኔን በመደገፍ የፀረ አማራ ወንጀሎች ተባባሪ ከመሆን አያመልጡም። በኦሮሞ በኩል ኦህዴድና ኦነግ ዋና የአማራ ጠላቶች ናቸው። እነዚህ የኦሮሞ የናዚ አቋም ያላቸው ድርጅቶች አማራውን ለመምታት በትጥቅ መደራጀቱ ንአጠናክረው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። አማራ ምሁራን ወይ፣ ዝምታችሁ መጨረሻው *"ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ"*

ሳይሆን ባስቸኳይ አማራ አድን ድርጅት ህያው እንድታደርጉ አለኝታ የሚሆነው ወገናዊ ተሚጋች ባጣው ህዝብ ስም ታሪካዊ ጥያቄና ጥሪ ቀርቦላችኋል።

በአማራነት ብቻ በወያኔ የሚፈሰው ደም በርክቷል። ይህ ፅሁፍ ባገራቸው ባይተዋርና ፪ኛ ዜጋ ሆነው ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸው በመጣስ ላይ ላሉት እናቶቼና አባቶቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ አጎቶቼና አክስቶቼ ለጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎና፣ ሽዋ አማራዎች በማስታወሻነት ያቀረብኩት ነው። የአማራ ተወላጆች በሙሉ ሁኔታው ብሶ ከቁጥጥር ውጪ ከመሆኑ በፊት እባካችሁ ***"የአማራ ድርጅት"*** የሚቋቋምበትን ሁኔታ ዕውን እናድርግ። አንገብጋቢና አስቸኳይ ጥሪ ነው። እስከ መቼ ድረስ የወያኔ፣ የኦነግ መጫወቻ የምንሆነው? ወያኔ የአማራውን ግዛት በተቻለው ሁሉ ጎማምዶ የተረፈውን የአማራ ክልል በሎ ለጥፎብናል። ኦነግ ደግሞ በከፋው የፋሽስት ፀረ አማራ አቋሙ በስተምስራቅ ሰሜን ሸዋን፣ ወሎን እወስዳለሁ ሲለን፤ በስተምዕራብ ደግሞ የጎንደርን ከሱዳን አዋሳኝ መሬቶች ለቤኒሻንጉል ሰጥቼዋለሁ በከፊል መተከልንም ለራሴ አድርጌዋለሁ ሰለዚህ ምን አባታችሁ ትሆናላችሁ ይለናል።

***"ውሀ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው"*** ኦነግ ጠንካራ መዋቅር አለው። የህዝብ ድጋፍም አልተለየውም። የኦሮሞ ምሁራን ከጎኑ ናቸው። ለመሆኑ ለአማራው ማን አለው? ውሎ አድሮ ሁኔታው አግጦ ሲመጣ አማራውን የሚያድነውስ አደራጅ ሀይል ከየት ይመጣል? **ከመቀደማችን በፊት በጥልቅ እስቡበት።** ***"ጉድና ጅራት ከበስተጀርባ ነው"*** ይባላል። እኛ አማሮችስ ምን ዝግጅት አለን? ***"ዝንጀሮ በቅድሚያ የመቀመጫዬን"*** እንደምትለው ሁሉ መላው አማራ ለአገሩ ኢትዮጵያ ሲያስብ የራሱን መቀመጫ ቤት በቅድሚያ ማመቻቸት ታሪካዊ ግዳጁ መሆኑን አጢኖ ማወቅ አለበት። የአማራ ምሁራን ነገር ***"ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ"*** ብቻ የሆነውስ ለምንድን ነው? ***"እኛ በዘር፣ በቋንቋ አናምንም"*** ትሉናላችሁ። እስቲ መላውን ኢትዮጵያ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። በዘርና በቋንቋ በአገር ውስጥም በውጪም ያልተደራጀ ያለ ይመስላቹሀል? እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራስ አድን ዘመቻ ውስጥ ሳይወድ ተገዶ ጭልጥ ብሎ ገብቶበታል። አማራጭ የለውም ምን አድርግ ትሉታላችሁ? አንድ መገንዘብ ያለባችሁ ነገር አለ። ኢትዮጵያን የሚወድ ሁሉ ትግሉንና መረባረቡን ምን ጊዜም አያቆምም። አማራው ብቻውን ደግሞ አገራችንን ኢትዮጵያን አያድንም። ወያኔ ጠንክሮ በመደራጀቱ እሱን መሰል ገንጣዮች፤ ጎጠኞችና ፋሺስቶች ሰብስቦ የፈለገውን ሰርቷል እየሰራም ይገኛል። ታድያ አማራው ራሱን አበርትቶ ከተንቀሳቀሰ እርሱን መሰል ኢትዮጵያዊ ወገኖች ማሰባሰብ ያዳግተዋል ያለ ማነው? አሁን ከሀያ ዓመት በላይ እስካሁን የተከተላችሁት በአገራዊነት ተደራጅታችሁ ያከሄዳችሁት ፀረ ወያኔ ትግል የትም አላደረሳችሁም። ***"አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው"*** ሀቅ ነው። የተረፋችሁ ነገር ቢኖር ***"የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች"*** ብቻ ነው።

ስለዚህ በቃን ብላችሁ የትግል ዘዴ መለወጫው ጊዜ አሁን መሆኑን ተገንዝባችሁ ***"የአማራ ብሔራዊ ሕብረት"*** ለማቋቋም መድረኮችን አዘጋጁ። ***"ምን ይዞ ጉዞ"*** ይባለል። ዛሬ በኢትዮጵያ ውሰጥ አማራ ላይ በወያኔና በደጋፊዎቹ የሚፈፀሙት የዘር ማጥፋት ወንጀሎች በረቀቀ ሁኔታ በዕቅድ በመካሄድ ላይ ይገኛሉ። በሐምሌ ፪ሺ፫ ብአዴን አዲስ ግብረ ሀይል አቋቁሟል። የሀይሉ ሀላፊነት በጭቆና ብዛት ከክልሉ በተለይም ከጎንደር፣ ከወሎና፣ ሰሜን ሸዋ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወደ ውጪ አገሮች የሚኮበልሉት አማራዎች ቁጥር የትዬ ለሌ እየሆነ በመሄዱ በተለይም በወጣቶች ላይ ልዩ ክትትልና ስለላ ማካሄድ መሆኑ ታውቋል። ወያኔም በአማራ ኮብላዮች መብዛት ተደናግጧል። የ.ተ.መ.ድ. ስደተኞች ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ከሚሰደዱት መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት አማራዎች እንደሆኑ አረጋግጧል። ዛሬ የብአዴን ካድሬዎች ከወያኔ በተሰጣቸው መመሪያ ዋነኛ ስራቸው ባቋቋሙት ግብረሀይል አማራውን ማዋከብና በተመረጡ ወረዳዎች ለምሳሌ በደባርቅ፣ በመተማ፣ በበየዳ፣ በጃንአሞራ፣ በቡልጋ፣ በአንኮበር፣

በመንዝና መርሀቤቴ፣ በወልድያ፣ በቆቦ፣ በሀብሩ፣ በወረባቦና በባቲ ላይ ክፉና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የክልሉንና የፌደራል ፖሊሶች፣ ካድሬዎች፣ የወያኔ አፋኝ ሰላዮችና የታጠቁ ሚሊሽያዎችን እንደ ንብ አፍሶ ከፍ ሲል በተጠቀሱት ወረዳዎች ኗሪ በሆኑትና ለአቅመ አዳም የደረሰ ወገንን ሁሉ መረጃ በማቀበል ተባበረን ተቃዋሚዎችን አጋልጥ በሚል እየተዋከበና ዘብ-ጥያ እየተወረወረ ኑሮው ***"ከሳት ወደ ረመጥ"*** ሆኖበት ይገኛል።

በአማራ ክልል በእሳት ጅራፉ ያልተቃጠለ ሰው ቢኖር ወያኔ በዘር ባቋቋማቸው ድርጅቶች ውስጥ አባል የሆነ ብቻ ነው። የአማራውን ጭቆና ይፋ በማድረግ በባለቤትነት በዓለም የሚንቀሳቀስ ድርጅት ባለመኖሩ የአማራው እሮሮ ተዳፍኖ ይብከነከናል። አይዞህ፣ አለሁልህ፣ ጭቆናህ ጭቆናዬ፣ በደልህ በደሌ፣ ጩኸትህ ጩኸቴ፣ ምዝበራህ ምዝበራዬ ብለው ለሕዝባቸው በአገርና በውጪ የሚታገሉና በማንነታቸውና በዘራቸው የማያፍሩ ድርጅቶችን በባዶ ሜዳ ከመናቅና የት ሊደርሱ ነው የሚለውን አቋም እርግፍ አድርጎ በመተው ***"ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሃል"*** ከሚለው ያባቶቻችን ምክር ተምረን እንነሳ። አለበለዚያ ***"ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ"*** እንደሚባለው ከስረን ሁሉን አጥተን መና እንዳንቀር የአማራ ***"ምሁራን"*** አስቡበት። በመጨረሻ ወያኔ በናንተ ትግል የሞተ ዕለት ሁላችንም በግባተ መሬቱ እንድንገኝ ለመላው አማራ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የነገ ሰው ይበለን። "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር።" በየድህረ-ገፆች፣ በጋዜጦችና መፅሄቶች፣ በቲቪና ራድዮኖች፣ በትምህርት ተቋሞች፣ በየስብሰባው መድረኮች፣ ለሰብዓዊና፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተቆርቋሪ ድርጅቶች፣ ለተለያዩ፣ ዓለም አቀፍ መዋቅሮችና መንግስታት የአማራውን ብሶት፣ ጭቆና፣ ምዝበራ፣ ጭፍጨፋ፣ ነፃነት አልባነት እንዲሁም አይ ዞህ ባይ አጥቶ መብቱን ተገፎ እንደሚኖር አሳውቁ። በኢንተርኔት የምተፅፏቸውን በወያኔው ገ/ፅዮን ገ/ሚካኤል የሚመራው የአይቲ ማፊያ ቡድን አገርቤት ላለነው እንዳይደርስ ቢያግዱትም ተስፋ ሳትቆርጡ ትግሉን አስፋፉ። አማራው በኢትዮጵያ የሚወክለው ወገን/ድርጅት እንደሌለው አውቃችሁ ሁላችሁም የአማራ ምሁራን በአደባባይ ትግላችሁን በቶሎ ሳይውል ሳያድር ሕሊናችሁን ***"በዘር አንደራጅም"*** ከምትሉት ጊዜ ካለፈበት ግትር አቋማችሁ አርቃችሁና አንፅታችሁ ተነሱ። አለበለዚያ ያ አስታዋሽና ወገን ያጣውን ጎንደሬ፣ ጎጃሜ፣ ወሎዬና ሸዌ ለዘላለም እስከ መጨረሻው መጥፊያው ድረስ እየተዋከበ ለሚደርስበት የወያኔ፣ ኦህዴድና ኦነግ ጭፍጨፋ እናንተም ብትሆኑ በበይ ተመልካችነት ተባባሪ ያደርጋችኋል። ካብራኩ የወጣችሁት የተሳሳተ የፖለቲካ ዘዴ፣ አቋምና አካሄድ ከሁሉም የከፋ ወንጀል መሆኑን ዕወቁት። በታሪክም በአደባባይም ከምናውቃቸው ጠላቶቻችንም በበለጠ ተጠያቂ የምትሆኑት እናንተ የአማራ ምሁራን መሆናችሁን አትጠራጠሩ። ለዘላለም ልቦናችሁ ሲጠይቃችሁ፣ ሲወቅሳችሁ ትኖራላችሁ። አንድ አዛውንት ያሉኝን ላካፍላችሁ ***"ትግሬዎቹ ለምለም የሆኑትንና የወርቅ ማዕድን ያላቸውን መሬቶች መርጠው ከጎንደርና ወሎ ሲወስዱ ዝምታ፣ ነዳጅ ዘየትም አላቸው የሚባሉትንም ለራሳቸውና ለሱዳን አሳልፈው ሲሰጡ ዝምታ፣ ሱዳኖች እኮ ወያኔ ጀግና እያለ በየለቱ የሚያሰለቸንን የአፄ ዮሐንስን አንገት የቀሉ ጠላቶች ናቸው። ለትግሬዎቹ ግን አማራው ከሱዳን የባሰ ጠላት ሆኖ ተወስዶ ነፃነቱን ተገፎ ሲረገጥ ዝምታ፣ እባክህ ተወኝየአማራ ምሁር አሞቱ ፈሷል"*** ብለው ተሰናብተውኝ ሄዱ። አባባላቸው ልጅ ሆኜ በደርግ ዘመን ይዘፈን የነበረውን ***"የማትረባ ፍየል ፀኝ ትወልዳለች ልጆቿም ያልቃሉ እርሷም ትሞታለች"*** እንዳስታውስ አደርጎኛል። እናንተስ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ ታውቃላችሁን? በበኩሌ በስደት ላለው የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳዮች ኮሚቴ ለሚያደርገው ሀቀኛ ስራ ከልቤ ሳመሰግን ባገር ያለነው ተበዳዮች ከአማራው የተወሰዱትን መሬቶች ምን ግዜም ከማስመለስ ወደኋላ የማንል መሆኑን ለማሳወቅ እወዳለሁ። ነገር ግን የናንተን ትብብር እንጠይቃለን።

## አስቸኳይ ጥሪ ለአማራ ተወላጆች በሙሉ!!

በመጨረሻ አስፈሪውን እውነታ አማራ ነን ለምትሉ ወገኖቼ ላሳያችሁ። የቅኝ ገዢዎች በፍልስጤም ሕዝብ ላይ ያደረሱትን ፍዳ ተመልከቱ። በ1949 እስራኤል ትቆጣጠረው የነበረው መሬት በሰሜን ምስራቅ ጥቂት ግዛት ነበር። በ1967 በምራበውያን ተጠናክራ በመገኘቷ አብዛኛው ፍልስጤም በእጇ ወደቀ። እስከ ቀይ ባህርና ከጋዛ በቀር መላውን የሜዴትራንያን ጠረፍ ያዘች። ፍልስጤሞች ተሰደዱ፣ አገር አጡ በጋዛና በዌስት ባንክ ብቻ ያለ ነፃነት ተከለሉ። ቀስበቀስም አብዛኛው ዌስት ባንክ በአዲስ መጤ ሰፋሪ እስራኤሎች መሬታቸውን እየተቀሙ ሄዱ። ዛሬ አማራው ላይ ተነጣጥሮ ያለው የሻቢያ፣ ወያኔና ኦነግ ዕቅድ ደረጃ በደረጃ መሬቱን በመቀራመት አገር አልባ ለማድረግ ነው። እጃችሁን አጣጥፋችሁ አማራዊ ድርጅት አያስፈልግም ብላችሁ እውቀታችሁን፣ ግዜያችሁንና ገንዘባችሁን አማራው ካለበትና አፍጥጦ እየመጣበት ካለው ጥፋት ለማውጣት ባላለመ *"ከራስ በላይ ነፋስ"* ከሚለው ሀቅ ውጪ ማበከሉን መቀጠላችሁ አገር ቤት ለሰለባው ተጋልጠን ላለነው *"በቡሀ ላይ ቆሮቆር"* ሆኖብናል። እባካችሁ ፈጣሪ ይለመናችሁ። *"ምን ይዞ ጉዞ"* የሚባለውን ታውቃላችሁ? ባገር ቤት ጠንካራ መሰረት የሌለው በውጪ የሚደረግ ትግል *"በድቡሽት ላይ የተሰራ ቤት"* መሆኑን ተረዱልን። ወያኔ ከ20 አመት በላይ ሲገዛ በቀልድ ወይም *"የትአባቱ የት ሊደርስ"* እያለ አይደለም። በቆራጥነት ይዞ የመጣውን የሕወሐት ማኒፌስቶ ተግባራዊ ለማድረግ ነው። ለዚህም አላማው የትግራይ ገበሬን፣ ሴት፣ ወንድ፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ፣ ታዳጊ ህፃናት፣ ደሀ፣ ከበርቴ፣ መሀይምና ምሁሩን አቅፎና መሰረት አደርጎ መንቀሳቀስ በመቻሉነው። የአማራ ምሁራን ግን እስካሁን ከዚህ ዋነኛ ጠላታችን ቅንጣት ያህል መማር አልቻላችሁም። መማርና መመራመር ውጪ ሄዶ መኖር አማራነታችሁን እንድትረሱና እንድትጠሉ ከሆነ፣ የአማራው ህልውና እየጠፋ ሲሄድ አማራዊ ድርጅት አያስፈልግም የምትሉት ጠላቶችን እያጠናከራችሁና አማራውን እያዳከማችሁ እየበጣጠሳችሁት መሆኑን እወቁልን። በኢትዮጵያ ስም አትደራጁ፣ አትታገሉ አይደለም የምንለው። የትግራይ፣ የኦሮሞ ሲዳማ፣ ጋምቤላ ወዘተ... ልጆች አገራዊ ፍቅርን መሰረት ባደረጉ ድርጅቶች አማካኝነት ተሰባስበው ትግል ውስጥ እንዳሉ ይታወቃል። ልዩነቱ እነዚህ ሰዎች ትግራዊ፣ ኦሮማዊ፣ ሲዳማዊ፣ ጋምቤላዊ ወዘተ... በሆኑ ድርጅቶችም በጣምራ የሚሳተፉ እንደሆነ ግልፅ ነው። አማራዊ ምሁራን ግን ከዚህ ካፈጠጠብን ሀቅ ጋር ተጋርጣችሁ መኖር መምረጣችሁ በራሳችሁ ህልውና ቁማር እየተጫወታችሁ መሆኑን አጢኑት።

ይህ ጽሁፍ በእጃችሁ ከደረሰ አባዝታችሁ ለሁሉም የአማራ ተወላጆች አከፋፍሉ። ቆሌ በራቃቸው ናዚ ዘረኛ ሴጣኖች የሚመሩትና አማራውን ለማጥፋት ተማምለውና ተገዝተው ያበሩብን ሻቢያ፣ ኦነግና ወያኔ ተጣልተው ሊጠፋፉ ነው ብላችሁ ራሳችሁን አትደልሉ። ኢትዮጵያን በተለይም አማራውን ራስ ራሱን በመቀጥቀጥ ለማዳከም አብረው ሰርተዋል። አሁንም ለይስሙላ ጠበኞች መስለው መሰሪ ዘረኛ ዕቅዳቸውን መተርጎሙን ተያይዘውታል። የአማራ ምሁራን ከእንቅልፋችሁ ንቁ። የቀን ህልማችሁን አስወግዱ። ለሰላም፣ ዲሞክራሲና ነፃነት በትጋትና ንቃት ታግላችሁ ለተገፋነው አማሮች በግፍ የተቀማነውን የዜግነት መብቶች ዳግም እንድንጎናፀፍ አለኝታ ሁኑን።

በአገር ቤት በደሉና ጭቆናው ካጎበጠንና በወያኔ በቁማችን እንደሞትን ከምንቆጠረው አደራጅ ብሎም የሚቀረቅርልን ወገን/ድርጅት አልባ አማራዎች አንዱ ነኝ።

ጤና ይስጥልኝ።